4ኛ ዓመት ቁጥር 42
4th year No. 42

ባህር ዳር ጳጉሜ 2 ቀን 1991 ዓ.ም.
Bahir Dar 7th Sep 1999

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKR HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 2.45	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠ ባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.O.BOX

ማ ው ጫ	CONTENT
አዋጅ ቁጥር 42/1991 የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ልማት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ገጽ 8	Proclamation N°42/1999 A Proclamation To Provide For The Establishment Of Micro And Small Enterprises Devlopment Agency page 8

አዋጅ ቁጥር 42/1991

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ልማት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የጥቃቅንና አነስተኛ አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ይበልጥ ማጠናከር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን በመገንዘብ፣

እነዚህ ድርጅቶች በኢኮኖሚው ውስጥ የበኩላቸውን ሚና ይጫወቱ ዘንድ ለማስቻል አስፈላጊውን እገዛና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች አራሱን የቻለ መንግሥታዊ ድርጅት ማቋቋም በማስፈለጉ፣

PROCLAMATION N° 42/1999

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF MICRO AND SMALL ENTERPRISES DEVLOPMENT AGENCY

WHERE AS, realizing that strengthening micro and small production and services rendering enterprises that are found in the region, has a great socio economic role.

WHERE AS, it has been found necessary to establish an autonomous governmental organization which facilitate the conditions by which those enterprises could at the necessary support to enable them to play their part in the economy

በአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ መንግሥት አንቀጽ 49/3/1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ "የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 42/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ
የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፡

1. " ጥቃቅን ንግድ ሥራ" ማለት የተከፈለ ካፒታሉ ከብር 20,000 ያልበለጠ የንግድ ሥራ ማለት ሲሆን ከፍተኛ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት ተቋማትን አይጨምርም::
2. " አነስተኛ ንግድ ሥራ" ማለት የተከፈለ ካፒታሉ ከብር 20,000 በላይ የሆነና ከብር 500,000 ያልበለጠ የንግድ ሥራ ማለት ሲሆን ከፍተኛ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት ተቋማትን አይጨምርም::
3. " ክልል" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ መንግሥት አንቀጽ 2 የተቋቋመውን የአማራ ብሔራዊ ክልል ነው::
4. "ድርጅት" ማለት የክልሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ልማት ድርጅት ነው::
5. "ቦርድ" ማለት ከክልሉ መንግሥት መ/ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጣ አባላት ያሉት የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ነው::

ክፍል ሁለት
ስለጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ልማት ድርጅት መቋቋም፣ ተጠሪነትና አደረጃጀት፣ ድርጅታዊ አቋም

NOW, THEREFORE, in accordance with article 49/3/1 of the constitution of the Amhara National Region, the following is proclaimed

PART ONE
GENERAL

1. Short Title
This proclamation may be cite as " The micro and small enterprises Development Agency establishment proclamation N^{o} 42/1999."

2. Definition
In this proclamation, unless the context other wise requires:

1."Micro Enterprise" means commercial enterprise whose capital is not exceeding Birr 20,000 other than technological and consultancy services.
2."Small Enterprises" means a business engaged in commercial activities whose capital is exceeding birr 20,000 and not exceeding 500,000 birr, other than high technological and consultancy service institutions.
3. " Region" means the Amhara National Region established in accordance with article 2 of the constitution of the region.
4." Agency" means Micro and Small Enterprises Development Agency of the Region.
5. "Board" means the managerial board of the agency constituting members from regional government institutions and the private sector.

PART TWO
Establishment, Accountability Organization And Structure Of The Micro And Small Enterprises Development Agency

3/ ስለ ድርጅቱ መቋቋምና ተጠሪነት

1/ የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ልማት ድርጅት ከዚህ በኋላ " ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2/ የድርጅቱ ተጠሪነት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል።

4/ የድርጅቱ አደረጃጀት

1/ የድርጅቱ ዋና መ/ቤት በባህር ዳር ከተማ ይሆናል።

2/ ድርጅቱ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ቦታ የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል።

5/ የድርጅቱ ዓላማ

ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች እንዲያድጉና እንዲስፋፉ፣ ለኢኮኖሚው ዕድገትም የበኩላቸውን ሚና ይጫወቱ ዘንድ አስፈላጊውን እገዛና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ማስተባበርና ድጋፍ ሰጭ ተቋማትን ማበረታት ይሆናል።

6/ የድርጅቱ አቋም

ድርጅቱ፣

1/ ከክልሉ መንግስት መ/ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጣ የሥራ አመራር ቦርድ፣

2/ በቦርዱ አቅራቢነት በክልሉ መንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣

3/ ሌሎች በየደረጃው የሚያስፈልጉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል።

ክፍል ሶስት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ልማት ድርጅት ጠቅላላ ሥልጣንና ተግባር፣

7/ የድርጅቱ ጠቅላላ ሥልጣንና ተግባር

ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት

3. Establishment and Accountability

1. "Micro and small Enterprise development Agency, here in after referred to as "The Agency" is here by established as an autonomous and legal organ pursuant to this proclamation.
2. The Agency shall be accountable to the executive committee of the Amhara National Regional State.

4. Organization

1. The head office of the agency shall be in Bahir Dar.
2. The Agency shall have branch offices established as may be necessary.

5. Objective

Facilitate the conditions by which micro & small enterprises can get the necessary support and assistance so that they can grow and expand, and play their part for development of the economy. Co-ordinate and encourage supporting institutions.

6. Structure

The Organization shall have :

1. A managing board constituted of members from regional government institutions and private sectors.
2. A General Manager to be appointed by the Regional state up on the recommendation of the board, and
3. Other staffs necessary on each level.

PART THREE

Powers and Duties of the Micro and Small Enterprise Development Agency of the Amhara National Regional State

7. Powers and Duties

The Agency shall have the following

ይኖሩታል::

1/የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎችን ዕድገት ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ የስልጠና ፍላጐቶችን ያጠናል፣ የሙያ ስልጠናዎች ይሰጣል::

2/ የሙያ ማሻሻያ፣ የቴክኒክና የሠርቶ ማሳያ ማዕከላት ያቋቁማል፣

3/ የድርጅቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችን ነድፎ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል::

4/ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች በክልሉ ስለሚያድጉበትና ስለሚስፋፉበት ሁኔታ ከፌዴራል ኤጀንሲና ከክልል መስተዳድር፣ ከሌሎች አካላትና ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል::

5/ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎችን ለማስፋፋትና ለማልማት የሚያስፈለጉ ተስማሚ የቴክኖሎጂና የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰባስባል፣ ያሠራጫል፣ የምክር አገልግሎትም ይሰጣል::

6/ የማምረቻና የገበያ ቦታዎችን እንዲሁም የብድር አገልግሎቶችን ለማስገኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያመቻቻል::

7/ የገበያና የንግድ ሥራ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናከርና በማሠራጨት፣ እንዲሁም የንግድ ትርዒቶችን በማደራጀትና በማስተባበር አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል::

8/ ስለ ክፍለኢኮኖሚው ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል ያሰራጫል::

9/ በጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች መካከል የእርስ በርስ ግንኙነትና የመረጃ ልውውጥ ቁርኝት የማድረግ አስፈላጊነትን ያስተዋውቃል::

10/ የጠቅላላ ጥራት አሠራርና አስተዳደር

powers and duties to:

1. Study, the demand necessary for training required to speed up the development of micro and small enterprises, and conduct training.
2. Establish skill up grading technical and demonstration centers.
3. prepare and submit to the board short, Medium and long-term plan of the agency and implement the same upon approval.
4. Develop relation with the federal agency, regional administration, other bodies and private sectors upon the conditions by which micro and small enterprises can grow and expand.
5. Prepare, collect and disseminate appropriate technologies and project profiles required for the expansion and development of micro and small enterprises, and provide consultancy services.
6. Facilitate conditions by which one can get manufacturing and marketing places as well as credit services together with other concerned bodies.
7. Render the necessary support by collecting, compiling and disseminating market and business activity information; as well as organize and coordinate trade exhibitions.
8. Collect, compile and disseminate other necessary information concerning the economic sectors.
9. Promote the importance of net working and exchange of information among micro and small enterprises.
10. Promote and enhance the concept of

316

316 ~~323~~

እንዲሁም በድርጅቶቹ መካከል በውል ሊፈጠር ስለሚችል የሥራ ቁርኝት አሠራር ያስተዋውቃል ያዳብራል።

11/ ለሚሠጣቸው አገልግሎቶች የአገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል።

12/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል።

13/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

ክፍል አራት

የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣ አወቃቀር፣ ስብሰባ፣ ተጠሪነት፣ ሥልጣንና ተግባር

8/ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አወቃቀርና የሥራ ዘመን

1/ቦርዱ ከክልሉ መንግሥት መ/ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ በክልሉ መንግሥት የሚሰየሙ ከሰባት እስከ ዘጠኝ የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል።

2/ ቦርዱ ሰብሳቢና ፀሐፊ የሚኖሩት ሲሆን የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በክልሉ መንግሥት የሚሰየም ይሆናል።

3/የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይወሰናል።

9/ የቦርዱ የስብሰባ ስርዓት

1/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ አማካኝነት በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

2/ ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፣

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ውሣኔ የሚሰጠው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል።

Development, Agency total quality management and sub contracting amalgaments among the Agencies.

11. charge fee for the services it renders.

12. Own property, enter in to contracts, sue and be sued in its own name.

13. Perform such other activities, which help to accomplish its objective.

PART FOUR

Members, Structure, Meeting, Accountability, Power and Duties of the Managing Board of the Agency

8. Structure And Term Of The Members Of The Managing Board

1. The Board shall constitute seven to Nine members to be assigned by the Regional state from government institution and the private sector
2. The Board shall have chairperson and secretary, and the chairperson shall be assigned by the state from among the members of the Board.
3. The term office of the member of the board shall be, decided by the executive committee of the region.

9. Meeting Procedure Of The Board

1. The board shall have a regular meeting once in every month; it may how ever, convene extra ordinary meetings up on the chairpersons call as deemed necessary.
2. There shall be a quorum where more than halves of the members of the board are present.
3. With out prejudice to the provisions of sub Article 2 of this article, the Board shall pass its decision by a simple majority vote. However in case of a tie, the chairperson shall have a casting

317

317

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ ሥርዓትና ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

10/ <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል::

1/ የድርጅቱን ሥራዎች የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እየመከረ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያስወስናል::

2/ የድርጅቱን የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ እንዲሁም ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት መርምሮ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል::

3/ የድርጅቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ መርጦ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያሾማል::

4/ ከተሿሚዎች በስተቀር ሌሎች ለዋና ሥራ አስኪያጁ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎች ምደባና ስንብት ያፀድቃል::

5/ ለዋናው ሥራ አስኪያጅ አጠቃላይ የሥራ መመሪያ ይሰጣል::

6/ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል::

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነት፣ ሥልጣንና ተግባር</u>

11/ <u>የዋና ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት</u>

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለክልሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለቦርዱ ይሆናል::

12/ <u>የዋና ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር</u>

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ላይ ለድርጅቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን

vote.

4. With out prejudice to the provisions of this Article, the Board may adapt its own rules and meeting procedures.

10. Powers and Duties Of The Board

The Board shall have the following powers and duties to:

1. Deliberate upon policy matters concerning the Agency's activities and submit proposals to the executive committee for approval.
2. Inspect and submit long and short term plans, annual work program and budget of the Agency to the regional executive committee, upon approval, supervise the implementation of the same.
3. Select and present the General manager of the Agency for appointment, to the executive committee of the Region.
4. Approve the assignment and dismissal of the officers of the Agency directly accountable to the General manager other than the appointees.
5. Give general directives to the general manager.
6. Submit timely reports to the Regional executive committee.

PART FIVE

Accountability, Powers And Duties Of The General Manger Of The Agency

11. Accountability Of The General Manager

The accountability of the General Manager of the Agency shall be to the executive committee of the Region and the Board.

12. Powers And Duties Of The General Manager

The general manager of the Agency shall, in addition to the powers and duties

በተጨማሪም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1/ የድርጅቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል::
2/ ከሹመት መደቦች በስተቀር ሌሎች የድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር፣ ምደባና ስንብት በሚመለከት ለቦርዱ አቅርቦ ያስፀድቃል::
3/ የድርጅቱን ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሳድጋል፣ ያሰናብታል::

4/ ለድርጅቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል::
5/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ድርጅቱን ይወክላል::
6/ የቦርዱን ውሣኔ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል::

7/ የድርጅቱን የየሩብ ዓመት፣ ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለቦርዱ ያቀርባል::

8/ ለድርጅቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈለግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል::
9/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

ክፍል ስድስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13/ በጀት
የድርጅቱ በጀት፣

1/ ከክልሉ መንግሥት ከሚመደብ፣ እና

2/ ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ ገንዘብ

vested to the agency as enumerated under article 7 of this proclamation, have the following powers and Duties to:

1. Direct, administer, and supervise the activities of the agency.
2. Submit to the board for approval, the employment, assignment and dismissal of the different heads of the agency other than the appointment posts..
3. Employ, administer, promote, and dismiss the employees of the agency in accordance with the civil services regulations.
4. Effect expenditure in accordance with the approved budget and plan of action of the agency, and supervise the implementation of the same.
5. Represent the agency, in its dealings with other 3rd parties.
6. Execute and cause the execution of the decision of the board
7. Prepare and submit to the Regional executive committee and the board, quarterly and annual activity performance and financial reports of the Agency.
8. Delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the agency, to the extent necessary for the efficient management of the authority.
9. Perform such other activities assigned by the board.

PART SIX
Miscellaneous provisions

13. Budget
The budget of the Agency shall be drown from:

1. The budget allocated by the regional state and
2. From other sources.

319

ይሆናል::

14/ <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

1/ ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል::

2/ የድርጅቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በክልሉ ዋና አዲተር መ/ቤት ወይም እርሱ በሚሠይማቸው አዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ::

15/ <u>ለድርጅቱ ሰለተላለፉ የሥራ ተግባራት</u>

ቀደም ሲል የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1988 መሠረት የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ለጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ልዩ ልዩ የድጋፍ ተግባራት እንዲሰጥ ተሠጥቶት የነበሩት ተግባርና ኃላፊነቶች በሙሉ ተጠቃለው በዚህ ድርጅት አማካኝነት እንዲከናወኑ ተላልፈዋል::

16/ <u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጐች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

17/ <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ጳጉሜ 2/1991 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት

14. Books of Accounts

1. the Authority shall keep appropriate and complete books of accounts
2. Financial documents of the Agency shall be, audited every year by the auditor general and other auditors to be assigned by it.

15. Duties Transferred To The Agency

All powers and responsibilities, which were previously given to bureau of trade and industry to give different supports to micro and small enterprises pursuant to proclamation that provides to establish and define the powers and duties of the executive organ of the Region Nº 4/1995, are here by transferred to the agency under this proclamation.

16.In applicable Laws

Any law, which is in consistent with this proclamation, shall not apply to matters provided for in this proclamation.

17. Effective date

This proclamation shall come in to force on the date of its publication in the Zikre Hig Gazette.

Done at Bahir Dar
This 7th day of September 1999
Council of the Amhara National Regional State

ባሕር ዳር ማተሚያ ቤት ታተመ